Title: Bete Debele and Alamu Dabi Interview

Creators: Debele, Bete; Dabi, Alamu; Bekele, Getnet

Date: June 7, 2012

City: Ejersa Gerro

Country: Ethiopia

African Oral Narratives: aodl.org/oralnarratives

እኔ ፕሮፌሰር ጌትነት በቀለ እባላለሁ እናንተም እራሳችሁን አስተዋወቃችሁኝ ወደ ጥያቄ እንገባለን፡፡

1. ለኬ ደምሴ እባላለሁ ነዋሪነቴ በኤጀርሶ ጅሩ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነው ከሀገር ውጭ ለጥናት የተፈለገውን ነገር ከኛ በፊት ከአባቶቻችን ጊዜ ጀምሮ ያለውን የምናውቀውን ለመግለጽ እሞክራለሁ፡፡
2. አለሙጣአ እባላለሁ በድርጅት ሥራ እሠራለሁ
3. ረጋሣ እባላለሁ በዚሁ ቀበሌ ነዋሪ ነኝ የልማት ቡድን ፀሐፊ ነኝ

ጥ. እዚህ አካባቢ ገበሬዎች የሚያመርቱት እህል ምንድነው ?

መ. ጤፍ ነው በአንደኛ ደረጃ በሁለተኛ ደረጃ ቦሎቄ በሶስተኛ ደረጃ ስንዴ

ጥ. ጤፍ መቼ ነው የሚዘራው?

መ. ከሐምሌ 5 እስከ ሐምሌ 29 ድረስ

ጥ. መቼ ይታጨዳል?

መ. አጨዳው ከጥቅምት 15 ጀምሮ ሲሆን እንደሚሬቱ ሁኔታ ይለያያል

ጥ. ቦሎቄስ መቼ ይዘራል?

መ. ከሰኔ 15 ጀምሮ ይዘራል

ጥ. መቼ ይታጨዳል?

መ. ከመስከረም 17 በኋላ ይታጨዳል

ጥ. ስንዴስ?

መ. ከሰኔ 15 እስከ ሐምሌ 2 መዝራት አለበት

ጥ. ታዲያ ገበሬዎች ለጤፍ፣ ለቦሎቄ፣ ለስንዴ ብለው የተለያየ መሬት አላቸው ወይንስ እንዴት ነው የሚዘሩት?

መ. እርሻው የቦሎቄና የስንዴ ከፍተኛ /ዳገታማ/ ውሃ መቋጠር የማይችለው ይዘጋጃል ለጤፍ ደግሞ ውሃ መቋጠር የሚችለው ተመርጦ ይዘጋጃል፡፡

ጥ. ጤፍ መጀመሪያ እዚህ አካባቢ ማን ሚዜስ እንደጀመረ ይታወቃል?

መ. አናውቀውም ድሮ አባቶቻችን ጤፍ በትንሹ ነበር የሚዘሩት በቆሎ ነበር የሚያመርቱ ለከብት ምግብነትም ስለሚያገለግል ድሮ ከአንድ ሄክታር በላይ አይዘራም ነበር በአሁኑ ወቅት ጤፍ አለህ ማለት ባንክ ገንዘብ አለህ ማለት ስለሆነ ሁሉም ጤፍ የሚያመርተው፡፡

ጥ. ገበሬዎች ያመረቱትን ጤፍ እንጀራ ይመገባሉ ወይንስ ለገበያ ብቻ ነው?

መ. አብዛኛው ለመሸጥ ነው የሚጠቀመው ጤፍ ነጭ ሠርገኛና ቀይ ጤፍ አለ ቀይጤፍ ለቀለብ ነው ነጭና ሠርገኛው ለገበያ ነው

ጥ. ጤፍ በብዛት እዚህ አካባቢ ሚዜስ የተጀመረው መቼ ነው በደርግ ዘመን ነው ወይስ በኢህአዴግ በግምት ልትነግሩኝ ትችላላችሁ?

መ. በኢህአዴግ ዘመን ነው በደርግ ጊዜ በማህበር ስለሚታረስ የግል ስላለነበረ የተመረተውንም ምርት እኩል ስለምትከፋፈል ጤፍ አይዘራም ኮታም ስለነበረ 20 ኩንታል ጤፍ ብታመርት 10 ኩንታል ይወስዱብሀል ስለዚህ ጤፍ ማምረት አይፈለግም፡፡

ጥ. ቦሎቄና ስንዴ ዕድሜው ስንት ይሆናል?

መ. ቦሎቄ አንደአየሩ ሁኔታ ነው ለምግብነት አንጠቀምበትም ስለዚህ እንደዋጋው ነው የምናርሰው ስራው ቀላል ነው ተባይም አይበዛበትም፡፡ ስለዚህ ቦሎቄ እንደዋጋው ሁኔታ ነው የምታርሰው፡፡ ስንዴ በአብዛኛው እዚህ አካባቢ አይታረስም ነበር፡፡ አሁን ግን በኢህአዴግ ጥናት ተደርጎ እዚህ አካባቢ ፋሚሊ የሚባለው ስንዴ ማምረት ጀምረናል በኛ አባቶች ጊዜ ግን ስንዴ አልነበረም፡፡

ጥ. በደርግ ጊዜ ጨርሶ አልነበረም?

መ. ነበር ግን እንደዚህ ሜሬት የሚይዝ ስንዴ አልነበረም፡፡ ዘርተንም የሚዘረዝርበት ጊዜ አለ አሁን ተጠንቶ ስለመጣ በደንብ ነው ስንዴ የሚሆነው

ጥ. ስለበቆሎ እሳቸው ጀምረውልን ነበር መቼ እዚህ አገር እንደተጀመረና እንደተስፋፋ ቢገልፁልን?

መ. በፊት በብዛት በቆሎ ይዘራ ነበር አባቶቻችን ከብት ስለሚያረቡ ለከብቶች መኖም ይጠቀሙበት ነበር፡፡ ለከብቶች መኖ በደንብ ሲያገኙ ሲጠቀሙ ወተት በብዛት ይገኛል፡፡ ወፍራም ሜሬት ስለሚፈልግ በብዛት ይመረት ነበር፡፡ አሁን ከብቶችም ስለሌሉ ወፍራም ሜሬትም ስለሌለ በቆሎ ማምረትን በስንዴ ተክተነዋል ስለዚህ በአሁኑ ሰዓት የበቆሎ እርሻ በትንሹ ነው ያለው፡፡ በቆሎ በብዛት ባይመረትም አሠራሩን ቀይረን እየሠራን ነው በቆሎ ምርት ሊቀንስ የቻለው ከብት ስለሌለ ነው፡፡ በቆሎ በሳይንሳዊ መንገድ በኮምፖስ አዘጋጅተን ለማዝራት ደግሞ ሳናስብ የአየሩ ሁኔታ ችግር አለ፡፡ በቆሎ በአባቶቻችን ጊዜ ሜሬቱ ለምነው ከብቶቹም አሉ ማዳበሪያ በከብት ፍግ ተጠቅመን እንዘራለን ሼየ የሚባል ዘር አለ እሱ በ3 ወር ተከሎ ይደርሳል፡፡ ካቱካና የምትባለው በ2 ወር የምትደርስ ግብርና አምጥቶ የምንጠቀምበት ነው አሁን ከብት ስለሌለ በኮምፖስ ተጠቀሙ ተብለን መንግስት ባደረገልን ምርምር እየተጠቀምን ነው ድሮ በአባቶቻችን ጊዜ የነበረው ዘር ሚያዝያ ይዘራል ዝናብ የሚችልም ነው የድሮወና የአሁኑ የተለያየ ነው ዘሩም አየሩም ተቀያይሯል፡፡ ሸዬ የሚባለው የበቆሎ ዘር ከሀረርጌ የመጣ ነው የመጣው አሁን የዝናቡ ሁኔታ እየቀነሰ ለሱ አልተስማማው ስለዚህ አሁን ካስሜ ዘር ነው የምንጠቀመው፡፡ በቆሎ በቴክኖሎጂ ሄደንበት በይበልጥ ለማስፋፋት የውሃ እጥረት አለ ስለዚህ ውሃ ለማቆር ፕላስቲክ ያልፈልገናል ፕላስቲኩም በተደጋጋሚ ጠይቀን ልናገኝ አልቻልንም እናንተ የምትረዱን ቢሆን ተደራጅተንም ቢሆን፡፡

ጥ. የበቆሎ ዘር ከሀረርጌ እንዴትና ማን እንዳመጣው ቢገልፁልን? በጣሊያ ጊዜ ጣሊያኖች ባደረጉት ጥናት ላይ የዚህ አካባቢ ሰው ከብት ማርባት እንጂ እርሻ አያርሱም ብለዋል? ይሄ ትክክል ነው?

መ. ዘሩን ከሀረርጌ ያማጡት ሰዎች ናቸው በአፄ ኃ/ስላሴ ዘመን ነው ጣሊያኖች ያሉት እውነት ነው ከብት ነበር ያለው እንዲያውም ዝሆንና አንበሳም ነበር ብለዋል፡፡ ጫካ ስለሆነ በዚያን ጊዜ አባቶቻችን እንደነገሩን ጣሊያኖች የፃፉት ትክክል ነው፡፡ በዛን ወቅት ብዙ ከብቶች ነበሩ በጣም ጫካ ስለሆነም አጥርም አያስፈልግም መውጫ የሚሆነውን ብቻ ዘግተን ነው እንጂ አጥርም የለ በዛን ወቅት ባንዳዎች ነበሩ እነርሱ ከብት ይዘርፉ ስለነበር እንዳይነኩ መውጫውን በሾክ ዘግተን ጫካ ወስጥ ነበር የምናሳድረው ይላሉ፡፡

ጥ. ስንት ከብት ነበራቸው አባትዎ?

መ. ከ70-80 ነበረ የአንድ አካባቢ ሰዎች አብረን ነበር የምንጠበቀውም በቆሎ የሚዘራውም ለከብቶች ሲባል ነበር

ጥ. ጫካው ምን ዓይነት ዛፍ ነበር በብዛት ያለው?

መ. ግራር

ጥ. እርስዎ ስንት ከብት አለዎት?

መ. 30 ይሆናሉ

ጥ. አሁን ደግሞ ስለሰዎች እናወራ እዚህ ያሉት ኦሮሞዎች የምን ጎሳ ናቸው ታውቃላችሁ አኗኗራቸውስ?

መ. አደራ በቹ፣ ጉኢ፣ ቂምቢቿ የሚባል ብዙ ጎሳ አለ ባጠቃላይ ግን ኦሮሞ ነው የሚባለው እሚዋሃውም በሽማግልና ነው የጠፉም የሚቀጣው በሽምግልና ነው አሁንም በአንድ ሰፈር ሰባት አምስት ሆነን ተመካክረን ነው የምንሰራው፡፡

ጥ. የጎሳም ስም ማን ነው ደብረዘይት አካባቢ ያሉት አዳ ነን ብለዋል የዚህ ማን ነው የሚባለው?

መ. አመጣጣችን ከበሸፍቱ አድአ ነው ይሄ አካባቢ ጫካና አንበሳ ነበረበት ቦታ ለማያዝ ጫካውን እያስፋፋን ነው የሚመጣውን ማንኛውንም ሰው ጎሳ አድርጎ እየያዘ ያለ ከቢሸፍቱ የመጣና በዚህ ኡሁ በወዲያ አድና ከፊንፊኔ ጀምሮ እስከ ወባ አሎጋ ድረስ

ጥ. ጊዜው ይታወቃል ወደእዚህ የማጡበት?

መ. ከታሪኩ እንደተረዳነው በጣሊያን ጊዜ ይመስለኛል

ጥ. ሉሜ ከየት ነው የመጣው?

መ. ሉሜ ማለት አመጣጡ ከግለሰብ ነው ሉሜ ሜቻ የሚሉ ታዋቂ ሰው ነበሩ እኛ ሰወዬ ታዋቂ ባላባት ናቸው ሉሜ ሜቻ ይባላሉ እስከ አባቱ አሁ ከሚል ጎሳ ነው የሚጠሩት በእሳቸው ስም ነው ሉሜ ተብሎ የተጠራው

ጥ. ሉሜ ሜቻ በየትኛው ዘመን ወይም ማን ውባላባት አድርጎ የሾማቸው መቼ ነው በህይወት የነበሩት?

መ. ትክክለኛዉ ጊዜ አይታወቅም

ጥ. ቱኬ ማማን ታውቃላችሁ?

መ. ቱኬ ማማ የአርሲ ባላባት ነበሩ

ጥ. እዚህ አካባቢ የሚቅለው ምን ምን ነው ጥራጥሬው?

መ. በእኛ አካባቢ ገብስ ባቄላ አተር ምስርና ሽምብራ ይሆናል /ይዘራል/

ጥ. እዚህ በብዛት ገበሬው የሚያመርተው ምንድን ነው? የግብርና ባለሞያ እንደመሆንዎ?

መ. ባቄላና አተር

ጥ. እዚህ አካባቢ ሽንኩርት የለም?

መ. በመስኖ ይጠቀማሉ

ጥ. የጠፉ የተተወ ሰብል አለ በፊት የነበረ አሁን የጠፉ?

መ. አለ፡፡ ዘንጋዳ በፊት ነበር አሁን ጠፍቷል ድሮ በማቢት ተዘርቶ 5 ወር ይፈጅበታል፡፡ ሀብታም የሚባለው የሚዘራው በዛን ዘመን ዘንጋዳ ነበር፡፡ አሁን አየሩ አልተስማማውም ጠፉ

ጥ. ስለ አየር ንብረት የምታውቁት የሙቀት ማጠን የዝናብ ሁኔታ አንድ ዓይነት ነው ከበፊቱ ጋር ወይስ ተቀያይሯል?

መ. አዎ ተቀያይሯል፡፡ ድሮ ቆላ ቢባልም እንደዚህ አይሞቅም ዝናቡም አሁን ወቅቱን ጠብቆ አይመጣም እንዳለ ነው የተቀያየረው ባለፈው ጥቅምት ዝናብ ጥሎ ነበር ቅዝቃዜው በጣም ሀይለኛ ነበር የደጋ እዚህ እንደዚህ አይቀዘቅዝም ነበር፡፡ ቆላም ቢሆን ለሊት ልብስ ለብሰን ነው የምናድረው አሁን ግን ልብስ ለብሶ የሚተኛ የለም ስለዚህ በአጠቃላይ ተቀያይሯል፡፡

ጥ. አፈሩ ለምነቱ ተቀይሯል?

መ. አዎ አፈሩ ለምነቱን አጥቷል የኛ ሀገር መሬት ወፍራም ነው አባቶቻችን መሬቱን ቀያይረው ነበር የሚዘሩበት መሬት ትርፍ ስለሆነ ችግር አልነበረም አሁን እሱ ጠፉ እንዲያውም ማዳበሪያ ለምነቱን አጠፉብን ብለን ማሰብ ጀምረናል፡፡

ጥ. አሁን ያለማዳበሪያ አትዘሩም?

መ. ጤፍ ያለማዳበሪያ ፈጽሞ እየዘራም ድሮ ያለማዳበሪያ ነበር የሚዘራው፡፡ እንዲያውም ግብርና ሚ/ር የአየር ሁኔታው ጋር የሚስማማ ምርጥ ዘር እያመጣልን ነው እንጂ በጣም ችግር ነው፡፡

ጥ. አንድ ሰው መጥቶ ገበሬው ካሉበት ችግሮች መካከል አንዱን ልፈታላችሁ እችላለሁ የሚፈታው ግን አንድ ብቻ ነው ቢል ዋና ችግራችን ብላችሁ የምትመርጡት ምንድነው?

መ. የአየር ሁኔታው ችግር ስለሆነ ኩሬ ማዘጋጀት አለብን ይህን ለማዘጋጀት ላስቲክ /ጀሪካል/ ያስፈልጋል ይህንን የሚረዳን ብናገኝ፤ የማዳበሪያ ችግር የማዳበሪያ ዋጋ መጨመርም ትልቁ ችግራችን ስለሆነ እነዚህን እንደ አንድ ችግር ቢያዙልን፡፡

ጊዜያችሁን መስዋዕት በማድረግ ለሰጣችሁን ማብራሪያ በጣም አመሰግናለሁ፡፡